FOUNDATION FOR BLACK COMMUNITIES
–
FONDATION POUR LES COMMUNAUTÉS NOIRES

# ብላክ አይዲያስ ግራንትስ፡ ብሪጅ ኤንድ ቢልድ 2023
# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

1. **ቢ3 (B3) ድርጅት ምንድን ነው?**

   **ጥቁር-መር ድርጅት፡** በሁሉም የአመራር እርከን ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ጥቁሮች ናቸው፤
   **ጥቁር-አገልጋይ ድርጅት፡** የድርጅቱ ዋና ግብ ትርጉም ባለው መንገድ ለጥቁሮች ድጋፍ መስጠትና ጥቁሮችን ማሳተፍ ነው፤
   **ጥቁር-ተኮር፡** አብዛኛው የፕሮግራም እንቅስቃሴዎች ቅድሚያ የሚሰጡት ለጥቁሮች አገልግሎት መስጠት ላይ ነው፤

2. **ድርጅታችን ሙሉ ለሙሉ ቢ3 እንደሆነ ተደርጎ ስለመታሰቡ እርግጠኞች አይደለንም። ድርጅታችን አንድ ወይንም ሁለቱን የቢ3 ቅድመ ሁኔታዎች ብቻ የሚያሟላ ቢሆንስ? ይሄ ማለት ድጋፉን ከማግኘት ያግደናል ማለት ነው?**

   የፋውንዴሽን ፎር ብላክ ኮሚዩኒቲስ (ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ./FFBC) ፈንድ አላማ፡ ጥቁር-መር የሆኑ ድርጅቶች፡ ከካናዳ ጥቁር ማህበረሰቦች (ኮሚኒቲዎች) ጋር ሆነብለውና አቅደው እንዲሰሩ ማገዝ ነው። እያንዳንዱን ማመልከቻና አመልካች ድርጅት ፕሮግራሙ ወይም ድርጅቱ ምን ያክል ከዚህ አላማ ጋር እንደሚጣጣም ወይንም አብሮ እንደሚሄድ እንመዝናለን። ሁሉም አመልካቾችም ድርጅታቸው እንዴት ጥቁር-መር እንደደሆነና ስራቸውም እንዴት በካናዳ ጥቁር ማህበረሰቦች ላይ በዕቅድ በጎ ተጽእኖ እንደሚኖረው ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

3. **ከዚህ ፈንድ የሚገኘውን ድጋፍ ከካናዳ ውጭ ላሉ ፕሮጄክቶች ማስፈጸሚያ መጠቀም እችላለሁ?**

   አይችሉም። ይህን ድጋፍ ማግኘት የሚችሉት ካናዳ ውስጥ ያሉ ድርጅቶችና ካናዳ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ብቻ ናቸው፡

4. **ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት ምንድን ነው?**

   ኢንኮርፖሬትድ-ያልሆኑ ድርጅቶች ማመልከቻቸው የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ ድጋፍ እንዲያገኝ ኢንኮርፖሬትድ የሆነ ለትርፍ ያልተቋቋመ ወይንም የተመዘገበ የበጎ አድራጎት ድርጅት በአጋርነት ሊኖራቸው ይገባል። ማመልከቻ ለማስገባት: ኢንኮርፖሬትድ የሆነ አጋር ድርጅት መኖሩን ማረጋገጥ ግዴታ አይደለም።

   ማሳሰቢያ፡ ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ኢንኮርፖሬትድ ከሆኑ አጋር ድርጅቶች አብሮ ስለመስራት መረጃና ድጋፍ ለአመልካቾች ለመስጠት ፈቀደኛ ሲሆን፣ ነገር ግን አጋር ድርጅት የማፈላለግና የማግኘት ሀላፊነትን ግን አይወስድም።



ኢንኮርፖሬትድ-ያልሆኑ አመልካቾች ለዚህ ዙር የድጋፍ ማመልከቻ፡ ኢንኮርፖሬትድ የሆነ አጋር ድርጅት እስከ ፌብሪዋሪ 15, 2024 ማግኘት አለባቸው። ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች ያሉትን ማስፈንጠሪያዎች (ሊንክ) በመጫን ማግኘት ይችላሉ።

a. ድርጅት ማስተዳደር፣ ኢማጅን ካናዳ
b. በጎአድራጎትና መስጠት የካናዳ መንግስት

5. **የኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅቱ ሥራውና ሀላፊነቱ ምን ይሆናል? ማመልከቻ የማስገባት እንቅስቃሴ ለመጀመር ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት የግድ ሊኖረን ይገባል?**

ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅቱ የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ.ን የድጋፍ ገንዘብ የመቀበል መብትና ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆነውን የቀረጥ ቅጾች የማስገባትና የገንዘብ አጠቃቀሙን ስሌት የማሳውቅ ሃላፊነት ያለበት ህጋዊ አካል ነው። ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅቱ ከኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድጋፍ ለሚጠይቀው ቡድን ሁለቱ ድርጅቶች በሚገቡት ስምምነት መሰረት ተጨማሪ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል። ማመልከቻ የማስገባቱን እንቅስቃሴ ለመጀመር ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት እንዳለዎት የማረጋገጥ ግዴታ የለብዎትም። ይሁን እንጂ ማመልከቻው ተቀባይነት አግኝቶ ድጋፍ እንዲያገኝ የግድ ኢንኮርፖሬትድ የሆነ አጋር ድርጅት ሊኖርዎት ይገባል። ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት ሳይኖራችሁ የድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ያስገባችሁ ከሆነ የገንዘብ ድጋፍ (ፈንዲንግ) ስምምነትና የትብብር ስምምነት ፈርማችሁን ፖርታሉ ላይ ማስገባት ይኖርባችኋል። ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት የሌላቸው አመልካቾች ድጋፍ ማግኘት አይችሉም።

6. **ኢንኮርፖሬትድ አጋራችን ቢ3 ድርጅት መሆን አለበት?**
ቢ3 የሆነ ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት ማግኘት ድጋፍ ለማግኘት እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን። ስለዚህም አጋር የሚሆነው ኢንኮርፖሬትድ ድርጅት ቢ3 መሆን አይጠበቅበትም።

7. **ኢንኮርፖሬትድ አጋራችን የንግድ ተቋም ሊሆን ይችላል?**
አይችልም። ኢንኮርፖሬትድ አጋር ድርጅት ለትርፍ ያልተቋቋመ ወይንም የተመዘገበ የበጎ-አድራጎት ድርጅት መሆን አለበት።

8. **ከአንድ በላይ ለሆኑ የድጋፍ ዘርፎች ማመልከት እችላለሁ?**
አይችሉም። አመልካቾች ለአንድ የድጋፍ ዘርፍ ብቻ እንዲያመለክቱ ይመከራሉ።

9. **ያለው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ምን ያክል ነው?**



- **መሰረታዊ የድጋፍ ዘርፍ** እስከ $40,000 ከፕሮግራም ጋር ያልተያያዙ መሰረታዊ ስራ ማከናወኛ ፍላጎቶች፤
- **የማሳደጊያ ድጋፍ ዘርፍ** ከ$40,000 እስከ $100,000 አዳዲስ ሀሳቦች ወይንም ከአሁን ቀደም ያሉ ሀሳቦችን ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ማስፋፊያ፤
- **የማህበረሰብ መዋዕለንዋይ (ካፒታል ) ድጋፍ ዘርፍ** እስከ $250,000 የሚደርስ ማህበራዊ መሰረታዊ ልማትና መዋዕለንዋይ ሥራዎች ማከናወኛ

10. **የማመልከቻ መራጮ ኮሚኒቲ ቡድን ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ብሆን፣ የራሴን ማመልከቻ ማንበብ እችላለሁ ማለት ነው?**

    አይደለም። የማመልከቻ መራጮ ኮሚኒቲ ቡድን ውስጥ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኛ አመልካቾች፡ የራሳቸውን ማመልከቻ አይገመግሙም።

11. **ከአሁን ቀደም ከኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድጋፍ ያገኘን ቢሆን፣ አሁንም ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት እንችላለን?**

    አዎን። ለዚህ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ።

12. **ለሰፖርቲንግ ብላክ ኮሚኒቲስ ኢኒሺዬቲቭ አመልክተናል። ለኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድጋፍ ማመልከት እንችላለን?**

    አዎን ማመልከት ይችላሉ። ለተመሳሳይ ስራ ድጋሚ ድጋፍ ማግኘት ግን አይችሉም።

13. **የማመልከቻ መራጮ ኮሚኒቲ ቡድኑ ውሳኔውን መቼ ያሳውቃል?**

    የመጨረሻው ውሳኔ የሚሆነው በማርች 2024 ማብቂያ ላይ ነው።

14. **ሀይማኖታዊ ተቋማት ማመልከት ይችላሉ?**
    አዎ ይችላሉ። ነገር ግን ሀይማኖታዊ ስራዎችና በምንም መልክ ለመሳተፍ የአንድ ሀይማኖት ተከታይ መሆንን እንደመመዘኛ ለሚጠቀሙ እንቅስቃሴዎች ድጋፍ አያገኙም።
    ምሳሌ: ሀይማኖታዊ ተቋማት ማህበረሰብን መሰረት ላደረገ የምግብ አገልግሎት (ኮሙኒቲ ኪችን) ቁሳቁስና ሰራተኛ ወጪ መሸፈኛ ድጋፍ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ዋና ተግባሩ ሀያማኖታዊ የሆነ እንቅስቃሴያቸው ግን ድጋፉን ማግኘት አይችልም።

15. **ማመልከቻዬን በተመለከ ጥያቄ ካለኝ ማግኘት ያለብኝ ማንን ነው?**
    ይህንን [የቀጠሮ መያዣ ገጽ] በመሙላት ከባልደረባዎቻችን ጋር ቀጠሮ ያስይዙ።



# የቃላት ማውጫ

የካናዳ የጥቁር ድርጅቶችና ጥቁር ማህበረሰቦችን ከሌሎች ለየት የሚያደርጓቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድጋፍ አሰጣጥም በማህበረሰብ እውቀት ላይ የተመሰረተ፡ ትምህርት-ተኮርና በሂደት የመሻሻል ይዘት ያለው ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ትርጓሜዎች አላማ ሀሳብን በሰፊው መረዳት እንዲቻል ለማገዝ እንጂ የማይለወጥ የመጨረሻ ትርጓሜዎች ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጁ አይደሉም።

**ጥቁር-ተኮር፡** አብዛኛው የፕሮግራም እንቅስቃሴ ለጥቁሮች አገልግሎት መስጠት ላይ ያተኮረ ነው።

**ጥቁር-መር ድርጅት፡** በሁሉም የአመራር እርከን ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ጥቁሮች ናቸው። (ይህም ማለት፡ ሠራተኞችን፣ የበላይ ሀላፊዎችንና አስተዳደሩን ያካትታል)።

**ጥቁር-አገልጋይ ድርጅት፡** የድርጅቱ ዋና ግብ ለጥቁሮች ትርጉም ያለው ድጋፍ መስጠትና ጥቁሮችን ማሳተፍ ነው፡ ፡

**የትብብር ስምምነት፡** የትብብሩን ሁኔታና አላማ በዝርዝር የሚያስቀምጥ የጽሁፍ ስምምነት ነው። ይህም ስምምነት የትብብሩን አላማ፣ የተባባሪዎቹን የስራ ድርሻና ሀላፊነት፣ የአሰራር አወቃቀርን፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትንና አልመግባባት ሲኖር ልዩነቱ እንዴት እንደሚፈታ ያሳያል። ይህ ስምምነት ለኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. በጋራ ማመልከቻ ያስገቡ አካላት በሙሉ ይፈርሙታል።

**ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ፡** ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የተመረጠ የህዝብ ተጠሪ፣ ወይንም እጩ የህዝብ ተጠሪ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም የሚደረግ እንቅስቃሴ።

**ዘላቂነት ያለው እድገት ግቦች (ሰስቴይነብል ዴቨሎፕመንት ጎልስ)፡** ዘላቂነት ያለው እድገት ግቦች በመባል የሚታወቁት የተባበሩት መንግስታት ድርጀት አባል መንግስታት ያቀዱትና ያዘጋጁት 17 አስቸኳይ እርምጃ ጥሪ ነው፡ ፡ ተጨማሪ መረጃ ከhttps://sdgs.un.org/goals ማግኘት ይቻላል።

**ጤና ላይ ወሳኝ ተጽእኖ ያላቸው ማህበራዊ ጉዳዮች (ሶሻል ዲተርሚናንትስ ኦፍ ኸልዝ)፡** የአለም ጤና ድርጅት እንደሚለው ጤና ላይ ወሳኝ ተጽእኖ ያላቸው ማህበራዊ ጉዳዮች ማለት “ከህክምና ውጪ የሆኑ ጤና ላይ ተጽእኖ ያላቸው ነገሮች” ናቸው። ተጨማሪ መረጃ እዚህ https://www.who.int/health-topics/social-determinants-of-health#tab=tab_1 ማግኘት ይቻላል።



FOUNDATION
FOR BLACK
COMMUNITIES
–
FONDATION
POUR LES
COMMUNAUTÉS
NOIRES

2 St-Clair Avenue East, Suite 300 | Toronto, ON, M4T 2T5 | forblackcommunities.org

1.833.442.5225 | info@forblackcommunities.org

